

1-2

# እምነት የጸሎት ቁልፍ ነው

ጸሎት አስማት አይደለም። ወይንም “አንድ ነገር” ተጭነን “አንድ ነገር” የምናገኝበት ዘዴ አይደለም። ጸሎት ነፍስ ባለውና ነፍስ በሌለው መካከል የሚደረግ ግንኙነት አይደለም። ነገር ግን ጸሎት ህይወት ባላቸው በሁለት አካል መካከል የሚደረግ ነው። ይኸውም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የሚሆን የተቀራረበ ግንኙነት ነው። እግዚአብሔር መኖሩን ከልባችን አምነን ካልተቀበልን ወደ እርሱ መጸለይ ከንቱ ድካም ብቻ ነው። ምክንያቱም ጸሎታችንንን አዳምጦ መልስ ሰጪ መኖር ስላለበት ነው። ለምሳሌ ስልክ አንስተን የፈለግነውን ቁጥር አዙረን፥ “ሄሎ” አንልም። የሚያዳምጠን ሰው ሳይኖር ስልኩን በጆሮአችን አድርገን በባዶ ሜዳ መነጋገር ቂሎች ያስኘናንልና ይህንን አናደርገውም። ነገር ግን በአእምሮአችን ያለውን ሰው ለማነጋገር የሰውየውን ቁጥር አውጥተን እንደውላለን። ለጸሎት ትክክለኛ መልስ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው፥ ጸሎቱን አዳምጦ እንደ አስፈላጊነቱ መልስ የሚሰጠው አምላክ እንዳለ ማመን አለበት። ጥንት አንዳንድ ሞኝ የግሪክ ሰዎች ጁፒተር የተባለውን አምላካቸውን ምስል ሲሰሩ ያለጆሮና ያለ አይን አድርገው ሰሩት። ለዚህ አምላካቸው የሚያቀርቡት ጸሎት “እግዚአብሔራችን ሆይ፥ ማንነትህንና ምንነህትን የማንውቅህ” በማለት ነበር። ይህንን ዓይነቱ ጸሎት ስልክ ደውሎ “ሄሎ ማንም ሁን ማንም ግድ የለኝም ብቻ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ” የሚለውን ዓላማ የሌለውን ሞኝ ሰውን ይመስላል። ያለማመን ከእግዚአብሔር ጋር ቅርብ ግንኙነት እንዳናደርግ ያደናቅፈናል። እንዲሁም በሌላ ወገን አዳማጭ እንዳይኖረን መሥመሩን ያፈራርሳል። ህያው መሆኑና ጸሎታችንን ሰምቶ መልስ የሚሰጠን መሆኑን ካላመንን መጸለይ ምን ይጠቅማል? እግዚአብሔርን በምድርም በዓየርም ፈለግሁት ግን አላገኘሁትም የሚለውን ሰው ለጸሎት ተንበርክኮ አናገኘውም። ምክንያቱም ከመጸለዩ በፊት በእግዚአብሔር ህያውነት ማመን ያለበት መሆኑን ስለምናውቅ ነው።

አንዲት እንግሊዛዊት ህጻን ልጅ የቀዶ ጥገና ህክምና እንዲደረግላት ወደ ሆስፒታል ገባች። ለቀዶ ጥገናው ዝግጅት እየተደረገ አስታማሚው መጥታ “አሁን እንግዲህ የቀዶ ጥገናው ከመደረጉ በፊት አንቺን በመድኃኒት እናስተኛሻለን” አለቻት። ልጅቷም “እንግዲያውስ የምታስተኙኝ ከሆነ አንድ ጊዜ ልጸልይ” ብላ ቀዶ ጥገና በሚደረግበት ጠረጴዛ ስር ተንበርክካ “ጌታ ሆይ አሁን ሀኪሞቹ ሊያስተኙኝ ነው፤ ሳልነቃ ብቀር ወይንም ብሞት ጌታ ሆይ ነፍሴን ለአንተ እሰጣለሁና ተረከበኝ’ ብላ ጸለየች። ከተንበረከከችበትም ሥፍራ ስትነሳ የሀኪሞችና የአስታማሚዎቹ ዓይንት በዕንባ እርሶ አየች። የቀዶ ጥገና ያደረገውም ሀኪም በዚህች ህጻን ልጅ ፍጹም የሆነ እምነት ምክንያት እቤቱ ገብቶ ለመጀመሪያ ጊዜ በእምነት ጸለየ። እንግዲህ ለጸሎታችን መልስ ለማግኘት በእምነት እንጸልይ። *“ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በዕምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባህርን ማዕበል ይመስላል”* ይላል ያዕቆብ 1፥6። እምነትን የተፈጥሮ ሕግ አያቆመውም። ሙሴ በዕምነት ውሃ እንደ ግድግዳ ቆሞ የእስራኤል ሕዝብ በቀይ ባህር በደረቁ እንዲያልፉ አደረገ። ጌዲዮን በሜድያውያን ላይ ድል ያገኘው በእምነት ነው። እንዲሁም በእምነት ኢያሱ የኢዮሪኮ ግንብ እንዲፈራርስ አድርጎ በጠላቶቹ ላይ ፍጹም የሆነ ድልን አገኘ።

# ጸሎት ከልብ ይፈልቃል

ጸሎት ምኞታችንን፣ አእምሮአችንንና ፈቃዳችንን የጠይቃል።

ሀ) ምኞታችን የታረመና የእግዚአብሔርን ፍላጎትና ፈቃድ ብቻ እንዲመለከት የተለማመደ መሆን እንዳለበት ያስፈልገናል።

ለ) አእምሮአችን ዓላማ ባለው ነገር ላይ መጸለይ እንድንችልና ሃሳባችን ሳይበታተን እንድንጸልይ ፍጹም የተዘጋጀ መሆን አለበት።

ሐ) ፈቃዳችን ደግሞ የጸሎትን ጥቅም በመረዳት ወደ ጸሎት ያዘነበለ መሆን አለበት።

# ጸሎት ለምን ይጠቅማል?

## 1) ከክርስቶስ ጋር ያቀራርባል

እግዚአብሔር ከሰው ጋር ህብረት ለመመሥረት ስለፈቀደ አንዱን ልጁን ወደ እኛ ላከው። በእርሱም በኩል የቀረበ ግንኙነት እንዲኖረን አደረገ ይህንንም አንድነታችንን ልናጠነክረው የምንችልበት መንገድ አንደኛው በጽሎት ነው። ሆኖም አሮጌው ተረጥሮአችን መጸለይ አይፈልግም። የምንፈልገውን ሁሉ ሰማያዊ አባታችን ሳንጠይቀው የሚያውቅ ከሆነ ለምን እንጸልያለን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ነገር ግን ጸሎትን የምንጠቀምበት የምንፈልገውን ነገር ለምነን ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ አንድነትና ህብረት ለመገንባት ጭምር መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ከእኛ ጋር ህብረት ለመፍጠር የልባችንን በር ለሚያኳኳው ጌታ መልስ ሰጥተን ልባችንን የምንከፍትለት በጸሎት ነው። ለማንም ክፍተን ያላሳየነውን የህይወታችንን አቋምና ይዞታ በጸሎት ጊዜያችን ለጌታ እናቀርበዋለን። ጸሎት በዚህ ዓይነት ዓለም ውስጥ ለሚኖሩት ክርስቲያኖች ፍጹም የሆነ ዕረፍት፣ ሰላምና ጸጥታን ይሰጣል። የወደፊቱን የዓለም ሁኔታ ስናስብ ያስፈራን ይሆናል። የሰማያዊው መስኮት ተከፍቶልን በመነጋገር ላይ ካለን ችግርም ሆነ መከራ እርሱ ራሱ በልባችን የተከለውን ሰላም ሊያጠፋ አይችልም። ስንጸልይ ሳለን ዓይናችንን በዙሪያችን ካሉት ሁካታዎች፣ ረብሻና ጭንቀቶች አንስተን ፍጹም ጸጥታና ሥርዓት ወደሞላበት ጌታ ብቻ አጥብቀ እንመልከት ነፍሳችንም ዘለአለማዊ ሰላም ወደ በዛበት ህይወት እንዲያተኩር ማድረግ ያስፈልገናል።

## 2) ሕይወትን ያነቃል

ዳዊት “ጌታ ሆይ ህዝቦችህ በአንተ ደስ እንዲለን አነቃቃን” ብሎ ጸለየ። መንፈሳዊ ሕይወቱ መነቃቃት እንደሚያስፈልገው ዳዊት የተገነዘበ ይመስላል። ለእኛም ጸሎት የመንፈሳዊ ህይወታችንን ማነቃቂያ ዓይነተኛ ቁልፍ ነው።

**በሚቀጥለው ክፍል፥ ፈቃዱን ማወቅ ይገባል፥ የሚለውን የመጨረሻውን ርዕስና ለውይይት**
**የሚረዱ ጥያቄዎችን ይዘንላችሁ እንቀርባለን። የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን።**
**አሜን!**